# የህግ የበላይነትና የሰብአዊ መብት ጥሰት

## ዋና ዋና ኹነቶች

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ፕሮጄክት መንግስታዊ ያልሆነ በአገር ውስጥ ያሉ የሰብአዊ መብት ድምጾችን ለማጉላት የተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ የሰብአዊ መብት መረጃዎች ላይ የሚያተኩር አድቮከሲ ተቋም ነው። ይህ ወርሃዊ የሰብአዊ መብት ዳሰሳችን ሲሆን የሚከተሉት ዋና ዋና ያለፈው ወር ላይ ያተኮርንባቸው ዋና ዋና የህግ የበላይነት የፓለቲካ እስረኞች አያያዝ እና የሰብአዊ መብት ጉዳዩች ናቸው ።

ሰኔ
2008

1

# ጋዜጠኛ ጌታቸው ሽፈራው የቀረበበትን ክስ ተቃውሟል

**“የፈፀምኩት ወንጀል የለም በነፃ ልሰናበት ይገባል” - ጋዜጠኛ ጌታቸው ሽፈራው**

**የወንጀል ዝርዝሩ በክሱ በደንብ ስለቀረበ መቃወሚያ ተከሳሹ ያስገበው መቃወሚያ ውድቅ መደረግ አለበት” - አቃቤ ህግ**



ህጉም ሳይፈቅድ ፍርደ ቤቱም ትእዛዝ ሳያስተላልፍ በማእከላዊ ፌደራል ወንጀል ምርመራ ከአምስት ወር ቆይታ በኋላ የሽብር ክስ ተመስርቶበት ወደ ኢዲስ አበባ ማረሚያ ቤት (ቅሊንጦ) የተሸጋገረው ‘የነገረ ኢትዮጵያ’ ዋና አዘጋጅ የነበረው ጋዜጠኛ ጌታቸው ሽፈራው የተመሰረተበትን ክስ ተቃውሞ ለፍርድ ቤቱ የክስ መቃወሚያ ባሳለፍነው ወር ሰኔ 1 ነበር ለፍርድ ቤት ያስገባው። ጋዜጠኛ ጌታቸው የቀረበበት የሽብር ክስ በፀረ ሽብር አንቀፅ 7/1 ሲሆን፤ ይህ አንቀፅ ‘በማናቸውም መልኩ በሽብር ተግባር መሳተፍ’ ሲሆን፤ ጌታቸው በመቃወሚያው ካነሳቸው ነጥቦች አንዱ “አንድ ሽብርተኛ ተብሎ የተሰየመን ድርጅት ስም መጥራት፣ የሽብር ድርጅቱ በሚጠቀምበት ሚዲያ መጠቀም ወይም የሽብር ድርጅት አባል ነው የተባለን ሰው ለሽብር ድርጅቱ አንዳችም ፋይዳ በሌለው ነገር ላይ ማነጋገር ሁሉ ይጨምራል በሚል ተለጥጦ መቅረብ የለበትም” ሲል የገለፀ ሲሆን፤ አቃቤ ህግ በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ስለነበሩ ክስተቶች የሽብር ድርጅት አመራር ናቸው ላላቸው ሰዎች መረጃ ማስተላለፍን በሽብር ድርጅቱ ውስጥ በማናቸውም መልኩ መሳተፍ እንደሆነ አድርጎ ማቅረቡ ስህተት ነው ሲል አመልክቷል። ላው አቃቤ ህግ “ተከሳሹ ከሽብር ቡድን ተልእኮ ተቀብሏል” ብሎ በክሱ የጠቀሰ ሲሆን፤ “ተልእኮ ከማን፣ መችና የት እንደተቀበለ በክሱ ስላልተጠቀሰ ይጠቀስ ሲል ጌታቸው ሽፈራው አመልክቷል። ጋዜጠኛ ጌታቸው ሽፈራው ላቀረበው መቃወሚያ በቀን 15/10/2008 አቃቤ ህግ ምላሽ የሰጠ ሲሆን “የቀረበው ክስ የህጋዊነትን መርህ በተከተለ መልኩ የቀረበ መሆኑን በመጥቀስ የወንጀል ድርጊቱ በማስረጃ የሚረጋገጥ ይሆናል በማለት መቃወሚያው ውድቅ ይደረግልኝ ሲል ለፍርድ ቤቱ አመልክቷል፡

፡ የተከሳሽን መቃሚያና የአቃቤ ህግን መልስ የተከታተለው የከፍተኛው ፍርድቤት 14ኛ ወንጀል ችሎት ለሃምሌ 15፣2008 ብይን ለመስጠት ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቶ ተከሳሹ በእስር ሆኖ የሚቀጥለው ቀጠሮ እየተጠባበቀ ይገኛል። የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብት ፣ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት እንዲሁም በህግ ፊት እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብቶች በዚህ ሂደት ተጥሰዋል፡፡

2

# አቶ ኦሞት አግዋ ለ8ኛ ግዜ ተቀጠሩ

**አቃቤ ህግ በምስክርነት ያስመዘገባቸው ግለሰቦች የውሃ ሽታ ሆነዋል**

አቃቤህግ ፍትህን የማስረፅ አላማ ካለው ምስክሮቹን ተከታትሎ የማሰቀረብ ኃላፊነቱን በአግባቡ ስላልተወጣ እንዲሁም ቀሪ ምስክሮቹ አስቀድሞ ከመሰከሩት ምስክሮች ጋር ተመሳሳይነት ያለው ጭብጥ ላይ የሚመሰክሩ ስለሆነ ብይን ይሰጥልን” ጠበቃ አምሃ መኮንን

የቀድሞው የአለም ባንክ የመብት ጥሰት አጣሪ ቡድን አስተርጓሚና የምግብ ደህንነት አራማጅ የሆኑት አቶ ኦሞት አግዋ ከስራቸው ጋር ለተያያዘ ስልጠና ወደ ኬንያ ሊጓዙ ሲሉ ከኤርፖርት ከተያዙ አመት ከሶስት ወር አልፏቸዋል። አቶ ኦሞት አግዋን ጨምሮ ሶስት ግለሰቦች በተጠረጠሩበት የሽብር ወንጀል እየተከራከሩ ሲሆን በቀን 02/10/2008 ቀሪ ምስከክሮችን ለመስማት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተገኝተው የነበረ ቢሆንም አቃቤ ህግ ምስክር አሟልቶ ማቅረብ አልቻለም። የተከሳሽ ጠበቃ የሆኑት አቶ አምሃ መኮንን ፍርድቤቱ የአቃቤ ህግን ምስክር ለመስማት በተደጋጋሚ እንደቀጠረ አስታውሰው አሁን መጥተው የሚመሰክሩት ምስክሮችም ከዚህ ቀደም ከመሰከሩት ጭብጥ ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ በዚሁ ብይን ይሰጥልኝ ቢሉም አስተያየታቸው በፍርድ ቤቱ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ ምስክሮቹ በፖሊስ ተይዘው እንዲመሰክሩ ፍርድ ቤቱ ለሀምሌ 12/2008 ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል። በነኦሞት ክስ ፍርድ



ቤት የሚመላለሱት ሶስት የምግብ ዋስትና ባሞያዎች የአቃቤ ህግን ምስክሮች ለመስማት ብቻ ስምንት ጊዜ ፍርድ ቤት ተመላልሰዋል፡፡ የነኦሞት ፍርድ ሂደት የተያዙ እና የተከሰሱ ሰዎችን አፋጣኝ ፍትህ የማግኘት በግልጽ ሲጣሱ ታይተዋል፡፡

3

# የፖለቲካ እስረኞች ለብቻቸው በጨለማ ቤት ውስጥ እንዲታሰሩ ተደርገዋል

**ጥቁር ልብስ መልበስ እስረኛ ብቻ ሳይሆን እስረኛውን ሊጠይቅ የመጣ መልበስ አይችልም**

**“እስረኞችን ታሳድማላችሁ” የእስር ቤቱ ሃላፊዎች**

በሽብርተኛነት ከተፈረጁ የሽብር ድርጅቶች አባልነት ስም የሽብር ክስ ተመስርቶባቸው በቂሊንጦ በእስር ላይ የሚገኙ የፖለቲካ እስረኞች “እስረኞችን እያሳደማችሁና እያሳመፃችሁ ነው።” በሚል ምክንያት ለብቻቸው ተገለው እንዲታሰሩ ተደርጓል። አቶ በቀለ ገርባን ጨምሮ ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች በጨለማ ቤት በእስር ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ ከዚህ ቀደም ኦሮሚያ ላይ በተከሰተው ህዝባዊ አመፅ ምክንያት በመንግስት ታጣቂዎች የተገደሉ ሰልፈኞችን ለማሰብ ፍርድ ቤት ጥቁር ልብስ ለብሰው ሊወጡ ሲሉ በማረሚያ ቤቱ ሰዎች “ጥቁር ልብስ ለብሳችሁ መሄድ አትችሉም” ተብለው ፍርድ ቤት ከመቅረብ የተከለከሉ ሲሆን፤ በተከታዩ ቀጠሮ ተከሳሾቹ ፍርድ ቤትም በባዶ እግራቸውና በውስጥ ልብስ መምጣታቸው ይታወሳል። በወቅቱም ሰብሳቢ ዳኛ ታረቀኝ የእስረኞቹን አቤቱታ ሰምተው በጽሁፍ እንዲያቀርቡ እና ለተጨማሪ ለሰብአዊ መብት ኮሚሽን ማመልከት ትችላላችሁ የሚል የፍርድ ቤቶች ስልጣን መሸርሸር የደረሰበትን ደረጃ በግልጽ ያሳየ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ እስረኞች የተያዙ እና የተከሰሰሱ ሰዎች ህገ መንግስታዊ መብቶች (ክብራቸውን በጠበቀ መልኩ መያዝ ፣ ከኢሰብአዊ አያያዝ መጠበቅ ...)በከፍተኛ ሁኔታ እየተጣሱ እንደሆነ የነአቶ በቀለ ገርባ የእስር እና የክስ ሂደት የወሩ እውነተኛ ማሳያ ነው፡፡

4

# የሰማያዊ ፓርቲ የጎንደር አስተባባሪ የቀረበብህን ክስ ተከላከል ተባለ

**ለተከታታይ ሰባት ቀን የርሃብ አድማ አደርጓል**

**“ቀጣይ ቀጠሮ ላይ እሬሳዬ ነው የሚመጣው” አቶ አግባው ሰጠኝ**

የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 14ኛ ወንጀል ችሎት በእነ ጌታቸው መኮንን የክስ መዝገብ በሽብር ተከሰው ከአመት በላይ ጉዳያቸው ሲታይ የነበሩ 16 ግለሰቦች ላይ የአቃቤ ህግ ምስክሮች ላይ ብይን ያስተላለፈው ባሳለፍነው ወር ነበር። ፍርድ ቤቱ በሰጠው ብይን መሰረት ከተከሳሾቹ መሃል አቶ ዘሪሁን በሬ፣ ወርቅዬ ምስጋነውና አማረ መስፍን ክሳችሁን መከላከል ሳያስፈልጋችው በነፃ የለቀቃቸው ሲሆን የሰማያዊ ፓርቲ የጎንደር አስተባባሪ የሆነው አግባው ሰጠኝን ጨምሮ 13ቱ የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ፍርድ ቤቱ አዟል። በተያያዘ ዜና አቶ አግባው ሰጠኝ “ብሔሬን መሰረት ያደረገ በደል እየደረሰብኝ ነው” ብለው ለፍርድ ቤቱ ቅሬታቸውን ገልፀዋል። “ዘረኛ ብለህ ሰድበህናል” በሚል ምክንይት እንግልትና ስቃይና እንግልት እየደረሰባቸው እንደሆነ የገለጹት አቶ አግባው ከጨለማ ቤት መውጣት የማይችሉ፣ ቤተሰብ ጋር የማይገናኙ ከሆን በጀመሩት ረሃብ አድማ እንደሚቀጥሉ ገልጸው በሚቀጥለው ቀጠሮ “ሬሳዬ ሊመጣ” ይችላል ብለዋል፡፡ እስረኞች በተደጋጋሚ የሚያቀርቡዋቸው የመብት ጥሰት አቤቱታዎች መጣስ እና የፍርድ ቤቶች ለዚህ መፍትሄ መስጠት አለመቻላቸው በአቶ አግባው ሰጠኝ ጉዳይ ላይም በድጋሚ በጉልህ ታይቷል፡፡



5

# የኦፌኮን አመራር የሆኑት አቶ ደስታ ዲንቃ በሽብር ተከሰሱ

**ለ6 ወራት የገቡበት ሳይታወቅ በማእከላዊ ምርመራ ቆይተዋል**

**“ወጣቶች በእድር ሽፋን ተደራጅተው አመፅ እንዲያስነሱ መመሪያ ሰጥተዋል”**

የኦፌኮን አመራር አባል የሆኑት አቶ ደስታ ዲንቃን ጨምሮ 4 ግለሰቦች በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 19ኛ ወንጀል ችሎት በቀን ሰኔ 7 ቀርበው አቃቤ ህግ የመሰረተባቸው የሽብር ክስ ተነቦላቸዋል። አቃቤ ህግ ተከሳሹን በሰሜን ሸዋ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ግንደበረት፣ ጀልዱ እና አካባቢው ያሉ ወጣቶችን በእድር ሽፋን ተደራጅተው አመጽና ሁከት እንዲያስነሱ ተልዕኮ ሰጥተዋል ሲል ይወነጅላል። የአቶ ደስታ ዲንቃ ክስ ከሌላው የኦፌኮን አመራር አባል ከሆኑት ከነበቀለ ገርባ ጋር የሽብር ክስ ተመስርቶባቸው በእስር ላይ የሚገኙት ጉርሜሳ አያኖ ጋር የተገናኘ ሲሆን፤ ተከሳሹ በመስከረም 2008 ዓ.ም ከጉርሜሳ አያኖ ጋር በመሆን በኦፌኮ ጽ/ቤት ወጣቶችን በመሰብሰብ መንግስትን ለመጣል “ባገኛችሁት መሳሪያ በዱላ፣ በገጀራ፣ በድንጋይ በመጠቀም ህዝቡን ነጻ አውጡ” በማለት የአመጽ ጥሪ አስተላልፈዋል ይላል። አቶ ደስታ የተከሰሱበት በፀረ ሽብር-አንቀፅ 4 እና 3 ንዑስ አንቀፅ 1 እስከ 6 ያለውን በመተላለፍ የሽብር ድርጊት ለመፈፀም ማሴርና ማቀድ ሲሆን ቀሪዎቹ 3 ተከሳሾች በፀረ-ሽብር አንቀፅ 7/1 በማንኛውም መልኩ የሽብር ድርጊት ውስጥ መሳተፍ በሚለው አንቀፅ ክስ ተመስርቶባቸዋል።

6

# የዮናታን ተስፋዬ የክስ መቃወሚያ ውድቅ ተደርጓል

**“ሀሳቤን በነጻነት የመግለጽ መብቴን ተጠቅሜ ጽፌያለሁ” አቶ ዮናታን**

**“በማስረጃ ምዘና የምናየው ይሆናል”**



አንድ ተከሳሽ ምስክር ከመደመጡ በፊት የቀረበበትን ክስ የመቃወም እድል እንዳለው በግልጽ በወንጀል ህጉ የተገለጸ ነው፡፡ በተከታታይ በፍርድ ሂደት ላይ ያሉ የፓለቲካ ጉዳዬች ግን ይህን የፍድ ሂደት ሲጠቅማቸው አይታይም፡፡ እስካሁን በክስ ሂደት ውስጥ ካለፉ አራማጆች ፣ ፓቲከኞች እና ጋዜጠኞች መካከል የክስ መቃወሚያ ተቀባይነት አግኝቶ ክስ እንዲሻሻል የተወሰነው በዞን9 ጦማርያን እና ጋዜጠኞች ጉዳይ ላይ ብቻ ነው፡፡ ከዚህም አልፎ ተቀባይነት የማያገኙት የክስ መቃወሚያዎች ጊዜ የማጓተት ተቃራኒ ተጽእኖ ማሳየታቸው የሰብአዊ መብት አራማጁ እና የሰማያዊ ፓርቲ የቀድሞ ህዝብ ግንኙነት ሃላፊው የወጣቱ የዮናታን ተስፋዬ ክስ በቂ ማሳያ ነው፡፡ ወጣቱ ፖለቲከኛ ዮናታን ተስፋዬ የክስ መቃወሚያ አስገብቶ በመቃወሚያው ላይ አቃቤ ህግ ያለውን መልስ ከሰጠ በኋላ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ብይን ለመስጠት ለሰኔ 14 ተቀጥሮ ነበር፤ በቀኑ ያዋለው ችሎት ተከሳሹ ያስገባቸው የመቃወሚያ ነጥቦች በፍርድ ቤቱ “በማስረጃ ዝርዝር ይታያል” ተብለው ውድቅ ተደርገዋል። በእለቱ ፍርድ ቤቱ የተከሳሹን የእምነት ክህደት ቃል የተቀበለ ሲሆን፤ ተከሳሹ “የተጠቀሰብህን ወንጀል ፈፅመሃል ወይስ አልፈፀምክም” ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ “ክሱ በቀረበበት መንገድ የተገለጸውን የሽብር ተግባር አልፈጸምኩም፡፡ ሀሳቤን በነጻነት የመግለጽ መብቴን ተጠቅሜ ግን ጽፌያለሁ፡፡ በመሆኑም የሽብር ተግባር አልፈጸምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም” በማለት የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡ ተከሳሹ በማረሚያ ቤት አያያዝ ላይ ቅሬታውን ለፍርድ ቤቱ ያስገባ ሲሆን፤ በጭለማ ክፍል ውስጥ ታስሮ እንደሚገኝ ገልጿል አጭር ቀጠር ተሰጥቶት ጉዳዩ ባፋጣኝ እንዲታይለት ቢጠይቅም ፍርድ ቤት የማረሚያ ቤቱ አስተዳደር በጉዳዩ ላይ መለስ እንዲሰጡ የአቃቤ ህግ ምስክር በሚሰማበት ቀን ሐምሌ 20 አዟል።

7

# ጋዜጠኛ ካሊድ መሃመድ እና ዳርሰማ ሶሪ የምስክሮች ማንነት ይጣራልን አሉ

**“ምስክሮቹ ሸጉጥ ይዘው ሲያስፈራሩን የነበሩ ሰዎች ስለሆኑ የምስክሮቹ ማንነት የጣራልን”**

በኢትዮጵያን ሙስሊሞች የተነሳውን የመብት ጥያቄ ተከትሎ መንግስት ከወሰዳቸው የሃይል እርምጃዎች መካከል የሀይማኖት መሪዎችንና የመብት አራማጆችን እና ጋዜጠኞችን ማሰር ነበር። ከነሱም መካከል ጋዜጠኛ ዳርሰማ ሶሪና ካሊድ መሐመድ ይገኙበታል። ጋዜጠኛ ካሊድ ማሕመድና ዳርሰማ ሶሪን ጨምሮ 20 ተከሳሾች ባሳለፍነው ወር ሰኔ 14 ቀር ምስከሮችን ለመስማት ፍርድ ቤት የተገኙ ሲሆን አቃቤ ህግ ሶስት ምስክሮችን በእለቱ አሰምቷል። በእለቱ የቀረቡት ምስክሮች ቤት ሲበረበር አይቻለሁ፣ ወረቀት ላይ ሲፈርሙ አይቻለሁ ብለው የመሰከሩ ሲሆን ተከሳሾቹ በእለቱ የተገኙት ምስክሮች “በማእከላዊ ሽጉጥ ይዘው ሲያስፈራሩን የነበሩ ግለሰቦች ስለሆኑ ማንነታቸው ይጣራልን’ ብለው ጠይቀዋል” ቀሪ ምስክሮች በተመለከተ በፖሊስ ተይዘው እንዲቀርቡ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቶ ለሐምሌ 7 ተለዋጭ ቀጠሮ ይዟል። አንደሌሎቹ ጉዳዮች ሁሉ የሁለቱ ጋዜጠኞች ጉዳይ በጣም እየተጓተተ ይገኛል፡፡

8

# በቀለ ገርባን ጨምሮ የኦፌኮን አመራሮች ላቀረቡት የክስ መቃወሚያ አቃቤ ህግ መልስ ሰጥቷል

**“የ85 ዓመት አዛውንት አያቴ 300 ኪሎ ሜትር አቋርጣ መጥታ ልታየኝ አልቻለችም” አቶ ደጀኔ ጣፋ**

**“በእስር ቤት መገለል እየደረሰብን ነው”**

**“እነ አቶ በቀለ ገርባ የማረሚያ ቤቱን ስም እያጠፉ ነው”**

የሽብር ክስ ተመስርቶባቸው በእስር የሚገኙት የኦፌኮን አመራሮች በአካባቢያችን የመዳኘት መብት አለን፣ እኛን የመዳኘትንም ስልጣን ያለው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው ብለው ላቀረቡት መቃወሚያ አቃቤ ህግ የፀረ-ሽብር አዋጅ አንቀፅ 31 ጠቅሶ የሽብር ወንጀልን የመዳኘት ስልጣን የተሠጠው ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድቤትና ለከፍተኛ ፍርድቤት ነው ብሏል። ሌላው የአቃቤ ህግ መልስ ተከሳሾቹ ላነሱት ‘በህገወጥነቱ በህግ ያልተደነገገን ተግባር እንደ ወንጀል ማቅረብ (Principle of Legality)’ ጋር በተያያዘ መልስ ሲሰጥ “ወንጀሉ በግልፅ በህግ የተቀጠ ነው፤ ማስተር ፕላኑን ሽፋን አርገው በህዝብና በንብረት ላይ ጉዳት አድርሰዋል፤ ባጠቃላይ ስርአትን በሀይል ለመናድ ሲነቀሳቀሱ የነበሩ ስለሆን ክሱ የህግን መርህ የተከተለ ነው” ብሏል በመልሱ።

ከማረሚያ ቤት አያያዝ ጋር በተያያዘ ተከሳሽ የኦፌኮ አመራር አባላት ጉርሜሳ አያና፣ ደጀኔ ጣፋ፣ አዲሱ ቡላላና በቀለ ገርባ ቅሬታ በፅሁፍ አቅርበዋል “በእስር ቤት መገለል እየደረሰብን ነው፤ ንጽህና በሌለውና ፍሳሽ በሚያስገባ ጨለማ ቤት ውስጥ ነው የታሰርነው፤ በዚህ ምክንያት ለጤና ችግር እየተጋለጥን ነው፤ ዓይናችንን እየታመምን ነው፤ እዚህ ለምንናገረው ስንመለስ የእስር ቤቱ አስተዳደር በቀል ይፈፀምብናል.....” ሲሉ የተናገሩት አቶ ደጀኔ ጣፋ በማስከተል “ይህ ፍርድቤት እውነት ጫና የሌለበት ከሆነ ችግራችንን ይፍታልን” ሲሉ በምሬት ተናግረዋል። የተከሳሾቹን አቤቱታ የሰማው ፍርድ ቤቱ በቀን ሰኔ 27 የማረሚያ ቤቱ ተወካይ መልስ እንዲያመጣ ባዘዘው መሰረት የማረሚያ ቤቱ ተወካይ ሶስት ገፅ የሚደደርስ መልስ ይዘው መጥተዋል። ይህ መልስ ተከሳሹቹ በማረሚያ ቤት ሰዎች ተፈፅሞብናል ካሉት በተቃራኒ እንደውም ተከሳሾች የሚወነጅልና ፍርድ ቤቱ ስርአት እንዲያሲዝለት የሚጠይቅ ነበር። “ጥቁር ልብስ እየለበሱ እስረኛ ሊያሳድሙ ሲጥሩ የነበረና ጥቁር ልብስ አትልበሱ ብለን ስንነግራቸው በውስጥ ልብስና በባዶ እግራቸው መጥዋል፤ ይህን ሁሉ ያደረጉት የተቋሙን ስም ለማጥፋት ነው። ስለዚህ ፍርድ ቤቱ ተከሳሾችን አደብ እንዲያስገዛ እንጠይቃለን” ብለዋል። ተከሳሾቹ ቤተሰብ እንዳያገኙ ተደርገዋል የሚለውን አቤቱታ ‘ሀሰት ነው’ ብለው የገለፀው ማረሚያ ቤቱ መልስ ሆኖም “ለጥበቃ የሚያመቻቸውን አሰራር አሁንም እንደሚቀጥሉበት” ገልፀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ የተከሳሾቹን አቤቱታና የማረሚያ ቤቱን መልስ ገምግሞ ብይን ለመስጠት ለሀምሌ 07 ቀን ተለዋጭ ቀጠሮ የሰጠ ሲሆን፤ የተከሳሹቹ መቃወሚያ ላይና የአቃቤ ህግ መልስ ላይ ብይን ለመስጠት ሐምሌ 25 የተሰጠው ቀጠሮ እንደተጠበቀ ይሆናል።

# የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ሪፖርት “የኢትዮጵያ መንግስት ንፁሃንን ገሏል” ይላል

**400 ኦሮሞዎች ተገለዋል ፤ በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ ታስረዋል**

**“የተገደሉት 172 ሰዎች ናቸው፤ የመንግስት ምላሽም ተመጣጣኝ ነበር” የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን**

9

የመንግስት የሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ የሰላ ትችን የሚሰነዝረው ሂውማን ራይትስ ወች ባሳለፍነው ሰኔ ወር አንድ ሪፖርት ለቋል። ሪፖርቱ ያተኮረው ካለፉት ስድስት ወራት ጀምሮ የተቀሰቀሰውን የኦሮምያ ህዝባዊ አመፅ ተከተሎ መንግስት በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ የወሰደው የህይል እርምጃ ላይ ነበር። ሪፖርቱ በመንግስት የፀጥታ ሀያሎች የተገደሉትን ሰላማዊ ዜጎች ምስል ይዞ የወጣ ሲሆን፤ 400 መቶ የሚደርሱ የኦሮሞ ተወላጆች መገደላቸውንና ከ10ሺ በላይ የሚደርሱ ደግሞ መታሰራቸውን ገልጿል። ሂውማን ራይትስ ዎች ከለቀቀው ሪፖርት ሁለት ሳምንት በፊት በአዋጅ የተመሰረተው የመንግስቱ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን በኦሮሚያ የተነሳውን ህዝባዊ አመፅ ተከትሎ ለመንግስት ያደላ ሪፖርት ያቀረበ ሲሆን፤ ለጠፋው ውድመት በዋነኛነት ሰልፈኞቹን አርጓል። ሪፖርቱ በአመፁ 172 ሰዎች በመንግስት ፀጥታ ሀይሎች መገደላቸውን የገለፀ ሲሆን መንግስት የወሰደውን እርምጃ “ተመጣጣኝ” በማለት ገልፆታል።

## አጫጭር መረጃዎች

- አሜሪካ ኤምባሲ ፊት ለፊት ሰላማዊ ሰልፍ ያደረጉት 20 የአዲስ አባባ ዩንቨርስቲ ኦሮሞ ተማሪዎች ለሐምሌ 4 ለብይን ተቀጥረዋል፡፡
- የወጣቱ ፓለቲከኛ ሃብታሙ አያሌው የጤና ሁኔታ አሳሳቢ ነው። የተሻለ ህክምና ለማግኘት ወደ ውጭ ጉዞውን አስመልክቶ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ቀጠሮ ሰጥቶአል፡፡
- ከእስር በነፃ የጸለቀቁት የዞን ዘጠኝ ጦማርያንና የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ላይ አቃቤ ህግ የጠየቀው ይግባኝ ብይን ለ2009 ዓ.ም ተሸጋገረ፡፡
- የዞን ፱ ጦማሪው በፍቃዱ ሀይሉ ‘አመፅ የማነሳሳት’ ክስ ብይን ለሐምሌ 29 ተቀጠረ፡፡
- ጋዜጠኛ ጌታቸው ሽፈራው በማእከላዊ ወንጀል ምርመራ ካለፍርድ ቤት ትእዛዝ መታሰሩን አስመልክቶ ምርመራ እንዲካሄድ የሚጠይቅ ክስ ለጠቅላይ ፍርድቤት አቀረበ።